
# ምዕራፍ አምስት

## የማስታወቂያ ጥቅም



**የሚጠበቁ ውጤቶች:**


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለ ማስታወቂያ ምንነት፣ ዓይነቶች፣ አስፈላጊነትና ጠቀሜታዎች ደረጃውን የጠበቀ ኢ.ምቋ በመጠቀም ታስረዳላችሁ፤
- ከማስታወቂያ ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው በዕለት-ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ከንባብ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ትለያላችሁ፤
- የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች በራሳችሁ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው መንገድ መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- የኢ.ምቋ የጥምር ምልክቶች አጠቃቀምና አፈጣጠር የኢ.ምቋ ሥርዓቶችን በመከተል በምሳሌ አስደግፋችሁ ትገልጻላችሁ::
- ከነጠላ ምልክቶች ጥምር ምልክቶች እንዲሁም ከጥምር ምልክቶች ነጠላ ምልክቶች ትገነባላችሁ፤
- የጥምር ምልክቶች አጠቃቀምና አፈጣጠር በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ።
- የኢ.ምቋ ምልክቶችን ሥነምልክታዊ ባሕርያትን ትተነትናላችሁ::

## ቁልፍ ምልክቶች




ድምጽ




ምስል




ሻጭ




ምርት




ብዙሃን መገናኛ




ማስታወቂያ




አምራች




ገዢ



ጋዜጣ




መጽሔት




ቴሌቪዥን




አገልግሎት




ሙያ



ትርፍ




ድርጅት



ማቋቋም



ራዲዮ



ደንበኛ



መረጃ

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## ዕይታዊ ንባብ

1. የሚከተለውን ሥዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።



2. በማስታወቂያዎቹ መካከል የምታዩትን የአቀራረብ ልዩነቶች አስረዱ።










# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ንባብ

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ውጭ ተሰቅለው ወይም በቴሌቪዥን ሲተላለፉ ከተመለከታችኋቸው ማስታወቂያዎች መካከል የወደዳችሁትን ወይም የጠላችሁትን አንድ ማስታወቂያ ምረጡና ለምን እንደወደዳችሁት ወይም ለምን እንደጠላችሁት ለክፈል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

2. ማስታወቂያዎች ጠቃሚ ወይም ጎጂ ናቸው ብላችሁ ታስባላችሁ? ለምን?

መምህራችሁ «የማስታወቂያ ጥቅም» የሚለውን ንባብ ሲያነቡ፣፣ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን-ለጎን፣ የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

## የማስታወቂያ ጥቅም

ማስታወቂያ፣ በድምፅ፣ በምስል ወይም በሁለቱም እየታገዘ የተለያዩ መረጃዎችን፣ አገልግሎቶችንና ምርቶችን ለማስተዋወቅ የሚጠቅም የንግድ ወይም የአገልግሎት ማስተዋወቂያ ዘዴ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ማስታወቂያን የሚያስነግሩት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ናቸው። ማስታወቂያው እንዲነገርላቸው የሚያደርጉትም ምርቶቻቸውና አገልግሎቶቻቸው ገዢ እንዲያገኙ ለማድረግ ነው። በማስታወቂያ አገልግሎቱንና ምርቱን የሚያስተዋውቀው አካል ለማስታወቂያው ይከፍላል፤ በማስታወቂያው መተላለፍ የሚፈልገውንም መልክት ያቀርባል። ማስታወቂያ በተለያዩ የብዙኃን መገናኛዎች ላይ ማለትም በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በቴሌቪ፫ንና በሬዲዮ እንዲሰራጭ ይደረጋል።

ማስታወቂያ ለአንድ ሀገር ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ በሀገራችን ራሱን የቻለ ማስታወቂያን የሚመለከት አዋጅ ነሐሴ 21 ቀን 2004 ዓ.ም ወጥቶ በሥራ ላይ ይገኛል። ይህ አዋጅ ቁጥር 759/2004 ሲሆን ስለማስታወቂያ የወጣ አዋጅ የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። የአዋጁ ዓላማ በመግቢው ላይ እንደተገለጸው ማስታወቂያ በምርት ግብዓት ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ረገድ ለሀገራችን ሁሉን አቀፍ እድገት አስተዋፅኦ የሚያበረክት በመሆኑ በምንከተለው ገበያ መር ሥርዓት ውስጥ ጤናማ የገበያ ውድድር እንዲኖር አስተዋፅኦው የጎላ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ በሥርዓት ላልተመራ ህብረተሰቡንና የሀገርን ገፅታ ሊጎዳ ስለሚችል የሚመራበት ሕግ አስፈላጊ መሆኑን ሕግ አውጪው ስላመነበት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

ማስታወቂያ፣ ምርት አቅራቢውንም ሆነ ተጠቃሚውን በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቅም ነው። ይኸውም በአንድ በኩል፣ አምራቹና አገልግሎት ሰጪው በማስታወቂያ በመታገዝ፣ ስለ ምርቱና አገልግሎቱ ጥራት፣ ብቃት፣ አስፈላጊነት፣ ጠቀሜታ እንዲሁም ምርቱና አገልግሎቱ ስለሚገኙበት ስፍራ ጭምር ስለሚገለፅ የምርቱን ገዢዎችና የአገልግሎቱን ተጠቃሚዎች ቁጥር ሊያሳድግ ይችላል። በሌላ መልኩ፣ በማስታወቂያ አማካኝነት ስለተለያዩ ምርቶችና አገልግሎቶች ስለሚናገር ተጠቃሚው የሚጠቅመውን መርጦ እንዲገዛ ዕድሉን ያሰፋለታል።

ማስታወቂያ የሚሠራው ለትርፍ ለተቋቋሙና ለትርፍ ላልተቋቋሙ ሁለት ዓይነት ድርጅቶች ነው። ለትርፍ የተቋቋሙ ድርጅቶች ማስታወቂያን የሚጠቀሙት ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን የሚገዙና የሚጠቀሙ ደንበኞችን በማብዛት ትርፋቸውን ለማሳደግ ነው። ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ደግሞ የሚያስተዋውቁት አገልግሎት ለማስተዋወቅና ተያያዥ መረጃዎችን ለማሕበረሰቡ ለማድረስ ብቻ ነው።

በአጠቃላይ ማስታወቂያ ስለ አንድ ምርት፣ አገልግሎት ወይም ስለአንድ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳይና ተግባር ለኅብረተሰቡ መረጃ የሚተላለፍበት ዘዴ ብሎ ማጠቃለል ይቻላል።

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ።**

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ንባብ ተወስደው ወደ ኢምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቋ አንብቡ።
2. መጽሐፎቻችሁን ሳትመለከቱ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ውስጥ በኢምቋ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ በኢምቁ መልሱ።**

1. ማስታወቂያ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ጠቀሱ።
2. አብዛኛውን ጊዜ ማስታወቂያን የሚያስነግሩት እነማናቸው?
3. ማስታወቂያ አስነጋሪዎች ማስታወቂያ እንዲነገርላቸው የሚያደርጉበት ምክንያት ምንድነው?
4. ኢትዮጵያ የማስታወቂያ አዋጅ እንድታወጣ ያሳሳት ምክንያት ምንድነው?
5. ስለማስታወቂያ የወጣው አዋጅ ዓላማ ምንድነው?
6. ሕዝቡ ከማስታወቂያ የሚያገኛቸው ጥቅሞች ምን እንደሆኑ አብራሩ።
7. አገልግሎት ሰጪዎች ማስታወቂያ በማስነገር የሚያገኟቸውን ጥቅሞች አብራሩ።

## መልመጃ ሦስት

### ዐረፍተ ነገር ምሥረታ

**የሚከተሉትን ቃላት የሚወክሉትን ምልክቶች በመጠቀም የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቁ መሥርቱ**

1. ብዙን መገናኛ
2. አምራች
3. ገገር

4. ድርጅት
5. ደንበኛ

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ምልከታ

### መልመጃ አንድ

የሚታዩ የተለያዩ ማስተወቂያዎችን በማጥናት በምን እንደተላለፉና፣ መልዕክቱን ለማስተላለፍ ምን እንደተጠቀሙ አጠር ያለ ዘገባ አዘጋጅታችሁ በክፈል ውስጥ በኢ.ምቋ አቅርቡ ።

### የቡድን ሥራ

በቡድን በመሆን፣ የማኅበራዊ ሚዲያና መገናኛ ብዙኃን የሚባሉትን ዝርዝር ለየብቻ ካዘጋጃችሁ በኋላ፣ በቡድን ተወካያችሁ በኩል በክፍል ውስጥ  በኢ.ምቋ አቅርቡ።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## የምልክቶች ትንተና

ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማራችሁት መሠረት፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና-ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ አሳዩ።



ምሳሌ:- **ድምፅ**

1. የእጅ ቅርጽ፡ ኅባጣ የእጅ ቅርጽ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ በጎሮሮ አካባቢ

3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውስጥ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ ወደ ፊት
5. በእጅየማይገለጹክፍሎች፡ ነፃ

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## ጥምር ምልክቶች ምሥረ

**ማስታወሻ**

### ጥምር ምልክቶች ምሥረታ

ጥምር ምልክት ማለት ሁለት የተለያዩ ምልክቶች በማጣመር የተፈጠረ አዲስ ትርጉም ያለው ምልክት ማለት ነው። ጥምር ምልክቶች በሚደረጉበት ጊዜ ተጣመሪ ምልክቶቸ ከነባራዊ ባሕርያቸው የተለየ የባሕርይ ለውጥ ይታይባቸዋል። ከነዚህም የእጅ እንቅስቃሴ ድግግሞሽ መቀነስ፣ በቀላሉ መዋሐድ፣ የመጀመሪያው ምልክት እንደተጀመረ የሁለተኛው ምልክት መኖርና ጥምረት በሚደረግበት ጊዜ በመካከላቸው ያለው ጊዜ አጠር ማለት። እንደ ሐረግ ተደርገው የሚወሰዱ ጥምር ምልክቶች አይደሉም።

**ምሳሌዎች**

1. ወንድ^ተመሳሳይ (የመስማማት ምልክት) = ወንድም

   (ወንድና ተመሳሳይ ምልክቶች ወደ ጥመር ምልክት ሲቀየሩ ተመሳሳይ የእጅ እንቅስቃሴ ድግግምሽ ይቀንሳል)
2. ቀይ^መክተፍ = ቲማቲም ( የሁለቱም ምልክቶች በቀላሉ ይዋህዳሉ)
3. ጥቁር^ከስር/ጎን = ጥላ (ጥቁርና ከስር መካከል አጭር ጊዜ ይኖራል)
4. ሥጋ^መስቀል(አንድ ነገር መስቀል) = ቋንጣ

## መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች የተቀመጡት ቃላት ከሁለት የተለያዩ ምልክቶች የሚሠሩ ጥምር ምልክቶችን የሚወክሉ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች ተጣመሪያቸውን እየፈለገችሁ በክፍል ውስጥ በኢምቋ አሳዩ።

1. ጠመኔ
2. ሐዋርያ
3. ዘላለም
4. ባል
5. ርካሽ
6. አስፓልት መንገድ
7. እህት
8. እርጎ
9. አለመስማማት
10. ሚስት

# ክፍለ ትምህርት ስድስት

## የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች ልምምድ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች ናሙናዎዎች በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ፣ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።

**ኢምቋ:** ማስታወቂያ ትርጉም ምን ድምፅ ፎቶ ወይም ሁለት መንገድ መጠቀም መረጃ ማስተላለፍ ምርት አገልግሎ ማስተዋወቅ መንገድ

**አማርኛ:** ማስታወቂያ፣ በድምፅ፣ በምስል ወይም በሁለቱም እየታገዘ የተለያዩ መረጃዎችን፣ አገልግሎቶችንና ምርቶችን ለማስተዋወቅ የሚጠቅም መንገድ ነው።

**ኢምቋ:** ብዙ ብዙ ጊዜ ማስታወቂያ መንገር መንገር ማ ነጋዴ

**አማርኛ:** አብዛኛውን ጊዜ ማስታወቂያን የሚያስነግሩት በንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ናቸው።

**ኢምቋ:** ነጋዴ ማስታወቂያ ምክንያት መንገር መንገር ምክንያት ምን ምርት አገልግሎት ማስተዋዋቅ ማስተዋወቅ መግዛት ሰው ማግኘት

**አማርኛ:** ነጋዴዎች ማስታወቂያው እንዲነገርላቸው የሚያደርጉት ምርቶቻቸውና

አገልግሎቶቻቸው ገገር እንዲያገኙ ነው።

**ኢምቂ:** መንግር ሕግ አለ ምን መጀመሪያ ማስታወቂያ መነገር ፈለገ ሰው ገንዘብ መክፈል እንደገና ማስተላለፍ ፈለገ ምን ዝግጅት ዝግጅት መሰጠት አለበት

**አማርኛ:** በማስታወቂያ አገልግሎቱንና ምርቱን የሚያስተዋውቀው አካል ለማስታወቂያው ይከፍላል፤ በማስታወቂያው መተላለፍ የሚፈልገውንም መልክት ያቀርባል።

**ኢምቂ:** ማስታወቂያ ማስተላለፍ መንገድ ልዩ ልዩ አለ ምሳሌ ጋዜጣ መጽሔት ቴሌቭዥን ሬዲዮ

**አማርኛ:** ማስታወቂያ በተለያዩ የብዙኃን መገናኛዎች ላይ ማለትም በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ እንዲሰራጭ ይደረጋል።